# የSwansea Mews የቦታ ዝውውር እውነታዎች

(ጁን 15፣ 2022)

ጁን 14 ላይ የቶሮንቶ ማህበረሰብ መኖሪያ ቤትዎች ለSwansea Mews ማህበረሰብ መደበኛ የዝውውር ሂደት ጀመረ።

ጁን 15 ላይ ለሁሉም ቤተሰብዎች የእጣ ቁጥር ለመስጠት TCHC የዘፈቀደ እጣ የሚያካሂድ ይሆናል። የዘፈቀደ እጣ ቁጥሩ የሆነን መኖርያ የመጀመሪያ አቅርቦት ማን እንደሚያገኝ ውሳኔ የሚሰጥበት ፍትሃዊ እና ግልፅ መንገድ ነው።

**የዘፈቀደ እጣ ቁጥሩ ጥቅም ላይ የሚውልበት ብቸኛው ጊዜ ከአንድ በላይ ቤተሰብዎች አንድ አይነት መኖርያን እንደ መጀመሪያ ምርጫቸው ሲመርጡ ብቻ ነው። ዝቅተኛ የእጣ ቁጥር ያለው ቤተሰብ መኖርያው ይሰጠዋል።**

ከዘፈቀደ እጣው በኋላ ተከራዮች ከቤተሰቦቻቸው ብዛት ጋር የሚጣመሩ መኖርያዎች ዝርዝር ይደርሳቸዋል፣ ወደየትኛው ክፍል ለመግባት እንደሚስማሙ በመረጡት ቅደም ተከተል ያስቀምጣሉ።

ተከራዮች ያሉትን መኖርያዎች እንደምርጫቸው ቅደም ተከተል ከዘረዘሩ በኋላ፣ TCHC የእያንዳንዱን ቤተሰብ ምርጫዎች ይገመግምና ይበልጥ ከሚመርጡት መኖርያ ጋር ያዛምዳቸዋል። እኛ ሁልጊዜ ለቤተሰቦች የመጀመሪያ ምርጫቸውን ለመስጠት እንሞክራለን።

አንድ ወይም ከዛ በላይ የሆኑ ቤተሰብዎች ተመሳሳይ መኖርያን እንደ መጀመሪያ ምርጫቸው ከመረጡ፣ መኖርያው ለየትኛው ቤተሰብ እንደሚሰጥ ለማወቅ የእጣ ቁጥሩ ጥቅም ላይ ይውላል።

TCHC ማጣመሩን ከጨረሰ በኋላ፣ ለተከራዮች እንዲጎበኟቸው ከመጋበዝ ጋር ለተጣመሩት መኖርያ የአቅርቦት ደብዳቤ ይደርሳቸዋል።

- ተከራዩ አቅርቦቱን ከተቀበለ፣ ለቦታ ዝውውሩ የሊዝ ውል ይፈርሙና TCHC እቅድን በማውጣት የማድረሻ ወጪያቸውን ይከፍላል።

- አቅርቦቱን ካልተቀበሉ ወደ ቀጣዩ የማጣመር ዙር እንዲቀላቀሉ ይደረጉና ሂደቱን እንደገና ይጀምራሉ።

**ምሳሌ፡-**

በአጠቃላይ ሶስት ቤተሰቦች የዝውውር ሂደት ውስጥ ይገባሉ፡- ቤተሰብ ሀ፣ ቤተሰብ ለ እና ቤተሰብ ሐ። ሁሉም ባለ ሶስት መኝታ መኖርያን ይፈልጋሉ።

በዝውውሩ መጀመሪያ ላይ ለሶስቱም ቤተሰቦች በዘፈቀደ የእጣ ቁጥር ተሰጥቷቸዋል፡-

ቤተሰብ ሀ – 2
ቤተሰብ ለ – 3
ቤተሰብ ሐ – 1

ከእጣው በኋላ ቤተሰቦቹ ያሉት ባለ ሶስት ክፍል መኖርያዎች ዝርዝር ይደርሳቸዋል።

ቤተሰብ ሀ እና ለ ሁለቱም 123 Pine Street'ን እንደ መጀመርያ ምርጫቸው አስቀምጠዋል። ቤተሰብ ሐ 456 Spruce Street'ን እንደ መጀመርያ ምርጫ አስቀምጠዋል። የምርጫው ግዜ ሲጠናቀቅ፣ TCHC የቤተሰብዎችን ምርጫዎች ይገመግማል።

456 Spruce Street'ን እንደ ዋና ምርጫቸው ሌላ ማንም ስላልመረጠ ቤተሰብ ሐ የመኖርያው አቅርቦት ይደርሰዋል።

123 Pine Street በቤተሰብ ሀ እና ቤተሰብ ለ እንደ መጀመሪያ ምርጫ ተቀምጧል። ለየትኛው ቤተሰብ መኖርያው መሰጠት እንዳለበት ለመወሰን TCHC የእያንዳንዱን ቤተሰብ የዘፈቀደ እጣ ቁጥር ያመለከታል። ቤተሰብ ሀ (2) ከቤተሰብ ለ (3) ያነሰ የእጣ ቁጥር ስላለው፣ ቤተሰብ ሀ መኖርያው ይቀርብለታል። ቤተሰብ ለ ሁለተኛ ደረጃ ላይ ያስቀመጡትን መኖርያ ይቀርብላቸዋል።